ስለ ፕሮፌሰር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ሞያና ታላቅነት ብዙ ተነግሯል። እኔ ከእሳቸው ጋር በሠራሁባቸው የመጨረሻዎቹ የሥራ ዓመታት በመ/ቤት ያየሁትን በአጭሩ አቀርባለሁ።

ፕሮፌሰር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ከውጭ አገር ወራሪዎችና ዘራፊዎች፣ ከልዩ ልዩ አራዊትና ከቤተ ክርስቲያን የዕቃ ግምጃ ቤት ቃጠሎ የተረፉን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት አብያተ ክርስቲያናት የብራና መጻሕፍትን ለማስቀረጽ ያቀዱት እንደ ዛሬ የአገራችን ተወላጆች ቤተ መቅደስን ባልደፈሩበት ጊዜ ነበር።

ይህም የሚያመለክተው የአገራቸውን የሃይማኖት መጻሕፍትና የታሪክ ሰነዶች ለመጠበቅ በአርቆ አሳቢነት ያወጡት ዕቅድ በመቶ ለሚቆጠሩ ዓመታት ሳይሆን በአየሺው ዘመን ለሚተኩት ዘመናት ነበር ማለት ይቻላል።

ፕሮፌሰሩ፣ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያን በማስፈቀድ በአደረጉት ጥረትና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት አብያተ ክርስቲያናት መልካም ትብብር ብዛት ያላቸውን የብራና መጻሕፍት በማይክሮፊልም አስቀርፀው በተለያየ መንገድ ከሚደርስባቸው ጥፋት አድነዋል።

እነዚያ በፊልም የተቀረጹትና ሌሎቹም ቀደምት የብራና መጻሕፍት በአሁኑ ጊዜ በየአብያተ ክርስቲያናቱ መኖራቸው ያጠራጥራል። በማይክሮፊልም የተቀረጹትን ግን ኮፒያቸውን ማትረፍ ተችሏል።

ሌላው ዐብይ ነገር ለምሳሌ፡

1. የአዲስ አበባ ቁስቋም ዕቃ ቤት ሲቃጠል ከ10 በላይ የሆኑ የብራና መጻሕፍት ተቃጥለዋል።
2. አዲስ አበባ የእንጦጦ ማርያም ዕቃ ቤት በሌቦች በመደፈሩ፡
   - ነገረ ማርያም
   - አርባዕቱ ወንጌል
   - ተአምረ ማርያም

   ጠፍተዋል።
3. በመንዝ ታላቅዋ የፍርኩታ ኪዳነ ምሕረት ገዳም 10 የብራና መጻሕፍት በሌቦች ተወስደዋል።
4. ከአንኮበር ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ከሃምሳ በላይ የብራና መጻሕፍት ሲዘረፉ የሣህለ ሥላሴ ንጉሠ ጀዋ የዘወትር ጸሎት ማድረሻ ዳዊት አብሮ ተወስዷል።

ታዲያ እነዚህ ከላይ በውድመትና በመጥፋት የተመዘገቡት የብራና መጻሕፍት ቀደም ሲል በማይክሮፊልም ተቀርጸው ስለ ነበር ፊልሞቻቸው በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲና ከፊልም በቤተ ክህነት ስለሚገኙ የፕሮፌሰር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ውለታ ሲታወስ ይኖራል።

ሆኖም ድርጅቱ እንደ እሳቸው ያለ ቀጣይ ሰው ባለማግኘቱ በደረሰበት ተጽዕኖ ለተወሰኑ ዓመታት ሲንገዳገድ ቆይቶ በ፲፱፻፹፩ ዓ. ም. ስለ ተዘጋ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የብራና መጻሕፍት ለከፋ አደጋ ተጋልጠዋል።

ፕሮፌሰር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ እያሉ በትርፍ ሰዓታቸውና ወደ ኢትዮጵያ የብራና መጻሕፍት ድርጅት ከተዛወሩ በኋላ ከ8000 በላይ የሆኑ የብራና መጻሕፍትን አንብበውና መርምረው ካታሎግ እያስገቡ በማይክሮፊልም እንዲቀረፁ አድርገዋል።

በዚያው የጥናት ጊዜያቸው የእየዘመኑን የእጅ ጽሑፍ አቀማመጥና የፊደላትን ቅርጽ የሚወክል፣ እንዲሁም ረጅም ዕድሜ ያላቸውን የዋየሎች ቅርፅ በተመለከተ በምርምር ከደረሱባቸው የብራና መጻሕፍት ከ፲-

፲፭ኛው ክ/ዘመን እንደ ተጻፈ የታመነባቸው የጣና ቂርቆስ ርቱዐ ሃይማኖትና የጉጉቤ መድኃኔ ዓለም መጽሐፈ ኢሳያስ ይገኙባቸዋል።

በርቱዐ ሃይማኖት ላይ ፕሮፌሰሩ ያካሄዱት የምርምር ውጤት በ፲፱፻፸፱ ዓ. ም. አፍሪካ ሆቴል በተደረገ ሲምፖዚየም የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን ጨምሮ ከተለያዩ ተቋማትና መ/ቤቶች፣ ከግል ደራሲያን በተወጣጡ ፻፶፫ የታሪክን የሥነ ጽሑፍ ምሁራን ሰፊ ውይይት ተርጎበት ጥናቱ ተቀባይነትን አግኝቷል። የጉባዔውም ውጤት የብራና መጻሕፍትን ማጥናትና ዕድሜያቸውን መወሰን የኢትዮጵያውያን የግል ስጦታ የመሆኑን ግንዛቤ አስፍቷል።

ፕሮፌሰር ሥርግው በምርምራቸው ውቅት ከተመለከቷቸውና አስተያየት ከሰጧቸው ሌሎች ቀደምት የብራና መጻሕፍት ውስጥ፦

1. ዓፄ ላሊበላ (1124-1160) ያጻፈው አርባዕቱ ወንጌል ዘቤተ መድኃኔ ዓለም፥
2. ዓፄ ዳዊት (1356-1386) በወርቅ ቀለም ያጻፈው ተአምረ ማርያም ዘግሸን ማርያም
3. ዓፄ ይስሐቅ ያጻፈው ምሥጢረ ሰማይ ወምድር ዘብርብር ማርያም፥
4. ዓፄ ዘርዐ ያዕቆብ (1428-1462) ያጻፈው መቅድመ ተአምረ ማርያም ዘግሸን ማርያም፥
5. አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ (1389-1462) ያጻፈው መጽሐፈ አቡሻህር ውይም ባሕረ ኃዛብ ዘርስጭ ጊዮርጊስ

እና ሌሎች በብዙ አርዕስት የተጻፉ የየዘመናቱ የብራና መጻሕፍት ናቸው።

ፕሮፌሰር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ከምርምራቸው አንዱ የሊቃውንትን ታሪክ ማጥናት ሲሆን የመምህራንን ቅኔ ለብቻ ይመዘግቡ ነበር። በተለይ የአለቃ ለማ ኃይሉን አንድ የዋዜማ ቅኔ በቃላቸው ስለ ያዙት ሊቃውተ ቤተ እግዚአብሔርን በተመለከተ በዘወትር ገጠመኛቸው ያነቡት ነበር።

ቅኔውም የሚከተለው ነው፦

<u>ዋዜማ ቅኔ</u>

*ኢይበቊዕ ክብረ ዘመድ እስመ ወልደ አብ ወድቀ በዕደ ኃያል ረኀብ።*
*አግብርት እንዘ ጽጉባን ወይተርፍ እክል።*
*ምሳሌ ዘኒ ነገር አጠየቀተነ ጎል።*
*አምጣነ ወልዳ ኢድኀነ እምለቢሰ ቈጽል።*
*እንዘ ወርቀ ትፈትል ድንግል።*

<u>ትርጉም</u>

*የእናትና አባት ሀብት (ክብር) አይረባም አይጠቅምም።*
*የባለፀጋው ልጅ ክርስቶስ ተርቧልና።*
*አገልጋዮቹ ጠግበው ምግብ ሲተርፋቸው።*
*የዚህንም ምሳሌ ሰበረት አይተናል።*
*ድንግል ወርቅ ስትፈትል ልጇዋ ቅጠል ከመልበስ አልዳነምና።*

ብለው ባለቅኔው ጌታ የተወለደ ዕለት በቅጠል መሸፈኑን ያመለክታል።

እኔም ከዚህ ቀጥዬ ከሰዓቱ አንፃር የእሳቸው የመረጡትን የዋዜማ ቅኔ ብቻ አቀርባለሁ።

<u>ዋዜም ቅኔ</u>

*ባሕረ ጥበባት ዘተሰምየ ሥርግወ ሥላሴ ዮሐንስ በማዕዶተ ባሕር ኀደረ።*
*ሕይወት ሐመረ ምሕዋሩ አኮኑ ተሰብረ።*
*ወመጻሕፍቲሁ ኵሎሙ ወዘበርዕሱ አግመረ።*

*ወረዱ ታሕተ ወተሰጥሙ ባሕረ።*
*እስመ ኮኑ ዝርዋነ ምድረ።*

*<u>አማርኛ</u>*
*ባሕረ ጥበባት የሚል ስም የወጣለት ሥርግወ ሥላሴ ዮሐንስ ከባሕር ምዶ አደረ።*
*ሕይወት መርከቡ ተሰብሯልና።*
*መጻሕፍቱና በራሱ ላይ የተሸከማቸው ሁሉ ወደታች ወርደው ከባሕር ውስጥ ሰጠሙ።*
*እንደ ትቢያ ተበትነዋል እና።*

**ሊቀ ጉባዔ ፈቃደ ሥላሴ ተፈራ**
**የፕሮፌሰር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ የሰማንያ ቀን መታሰቢያ**
**ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል**
**አዲስ አበባ**
**መጋቢት ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ. ም.**